ቀን

# የሀገር ጠላት ወያኔ

ትውልድ ሀገሬ ኢትዮጵያየ ሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ ያላትና የሥላጣኔ ምንጭ፤ የአፍሪካ የነጻነት መሪ በመሆን ታፍራና ተከብራ የኖረች ስትሆን፤ ይህችን ጥንታዊት ሀገር ለማጥፋት የተነሳው ሀገር በቀል ጠላት ወያኔ ህዝቦችዋን በጥባብ ጎሳዊ መድሎ /Inland partied/ እና ለም መሬት አሳልፎ ለባዕዳን በመስጠት ጥንታዊ ዳር ደንብርዋን በመሸራረፍ እዳልነበረች ለማድረግ ዕቅድና ኘላን ያወጣው ገና ከጂምሩ እራሱን የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር ብሎ የሰየመው በትግራይ ግዛት ወስጥ ደደቢት ተብሎ በሚጠራው ቦታ ነው።

ከዚህን ግዜ ጀምሮ ለአስራ ሰባት ዓመታት ባደረገው የጥፋት ዘመቻ በሀገርና በሀገር ወዳድ ወግኖች ላይ ከፍተኛ ጥፋት አድርስዋል። በተለይም በወቅቱ በሀገራችን የተከሰተውን ድርቅና ርሃብ ምክንያት እራሱን ብቸኛ የሕዝብ ተቆርቋሪ መስሎ በማቅረብ የዓለም ለጋሽ ሀገራትን በማታለለና በማጭበርበር በድርቁ በተጎዳው ወገናችን ስም ያገኘውን በመሸጥ እና የጦር መሳሣሪያ በመግዛት እራሱን ከማደራጀቱም በላይ እርዳታው እንዳይደርስ መሰናከል በመፍጠር ቦንብ በማፈንዳት ሀገርራችን እና ወገናችንን ለአደጋ የዳረገ ነው።

የዓለም ለጋሽ ሀገሮችን አጭበርብሮ ዕርዳታውን ያገኘው ነጻ አወጣሀለሁ በሚለው የትግራይ ሕዝብ ላይ በተለይም ሐውዜን በሚባለው የገበያ ቦታ ሕዝቡን ሰብስቦ ቅስቀሳ እንድሚያደርግ የተሳሳተ መረጃውን ለደርግ አሳልፎ በመስጠት፤ ደርግ ወንበዴውን ወያኔን እመታለሁ በሚል ስሜት ጭቁኑን በሐውዜን አካባቢ የሚኖረን የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለመግፋት ገብያ የወጣውን ሕዝብ በአውሮኘላን ቦንብ በማስደብደብና በመሬት እራሱ በመደብደብ የሰራውን የተቀንቅጀ ፊልም አስመስሎ በወቅቱ የነበረውን ገዥ መንግሥት ደርግን በዘር ማጥፍተ ወንጀል ተጠያቂ የሚያደርገውን የሐሰት ፕሮፓጋንዳ በከፍተኛ ደረጃ በማሰራጨት ነበር።

በዚህ ዓይነት የወንብደና ተገባር ሕዝብን እየጨረሰ፣ የመግስት ተቋማትን እያፈረሰ፣ የገበሬውን መሬት ቦንብ የቀበረ በታንክ እያረሰ ጊዜው ጠብቆ በተጭበረበረ መረጃ የዓለም መንግሥታትን እያሳመነ የኤርትራን ነጻነት አውጃለሁ ከሚለው አባቱ ሻብያ ጋር በመተባበር ወይም ገንጣይ እና አስገናጣይ በመሆን በአንድነት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የደርግን አገዛዝ አስወግዶ ያለሕዝብ ፈላጎትና ምርጫ በጦር መሳሪያ በኃይል አስገደዶ በተረመንግስቱን ጨበጠ ።

ከዚያም የመጀመሪያው ዓላማና ተግባሩ አፍሪካ በቀኝ ገዥዎች ከመበታተንዋ በፊት ለዘመናት በኢትዮጵያ ነገሥታት የኢትዮጵያ ግዛት ሆና የቆየችውን በኃላም ጣልያን ከሀገራችን ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በተለይም ብ1945 ዓ.ም በተደረገው ፌዴሽን ምክንያት በሕዝቡ ፈቃድና መርጫ ኤርትራ የኢትዮጳያ ግዛት ሆና ከቆየች ከአምሳ ዓመታት በኃላ የአሳዳጊው የሻብያ እጅ መንሻ በማድረግ ኤርትራን አስገነጠለ።

ቀጥሎም የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በራሳቸው በማጋጨትና በማጨፋጨፍ የሀገሪቱ በቸኛ ገዥ ሆኖ የብዙ ንጹሀን ዜጎችን ደም በከንቱ አፈሰሰ። በተለይም በደቡባዊ የሀገራን ክፍል በደኖ በተባለው ቦታ

ብዛት ያላቸው የኦረሞ እና የአማራ ተውላጆችን በመጨፍጨፍና ከነ ሕይወታቸው ገደል ውስጥ በመጣል ሰባዊነት የጎደለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሚል፤ለዚህም ምክንያት ያደረገው የኦሮሞ ነጻ አውጭ ገንባር ጨፈጨፋቸው የሚል የሐሰት ፓሮፓጋንዳ በማሰራጨት ነበር።

በሀገራችን ታሪክ በዚህ ዓይነት ወንጀል ማለትም በትውልድ ላይ የማይረሳው ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል Genocide የፈጸመ ቢኖር ወያኔና ወያኔ ብቻ ነው። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝናው በዓለም የታሪክ መድራክ ተመዝቦ በማይገኝ መለኩ የሀገሪቱን ታሪካዊ ግዛት አሳልፎ በመስጠትና ትገንጠል በማለት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ደብዳቤ ጽፎ ሀገር ያስገነጠለ ሀገር ጠላት የሆነው ወያኔ ብቻ ነው።

ይህ ታሪካዊ ጥፋት የሰው ልጅ ሕይዎት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮ ያደላት ኢትዮጲያ፤ ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ መሠረት ሰፊ ሚና የሚጫወተውን ከፈተኛ የንግድ ልውውጥ የሚደረገበትን የሀገራችን የአሰብን ወደብ ጨምሮ አሳልፎ የሰጠና ሀግሩቱን ወደብ አልባ ሀገር /Land locked Nation/ያደረገ ነው። ይህም ሚያሳየው ከላይ ለመጥቀስ እደተሞከረው የኢትዮጵያን የብሔር ብሔረስቦች ታሪካዊ አንድነት ከመበታተንና ሀገሪቱን ከጥፋት የመነጨ ተልዕኮ ነው።

ከዚህ ሁሉ ውንጀለኝናት በተጨማሪ ከአሳዳጊው ከሻብያ ጋር በጥቅም ባስነሳው ጦርነት በአፍሪካ በዓይነቱም ሆነ በይዘቱ እጅግ በጣም ከባድ የሆነ አላስፈላጊ ጦርነት በማንሳት ወደ ሰማንያ ሺህ የሚደርሱ ዜጎች ሕይዎታቸው ጠፍቷል፤ በቢሊዮን የሚቆጠር ንብረት ወድሟል፣ ንጹሀን ዜጎች ለስደት ተዳርገዋል።

የወያኔን አገዛዝ በመጥላት ሀገራችውን ጥለው የተሰደዱ ዜጎች ቀጥራቸው ከግምት በላይ ነው። በስደት ላይ በሊቢያ በርሃ የተገደሉና ልባቸና እኩላሊታቸው እየወጣ ለግብጽ ሆስጂታሎች የተሸጠ ዜጎች ቁጥር ብዙ ነው። በባህር ሲሻገሩ የአዞ ቀለብ ሆነው የቀሩት ዜጎቻችን ቀላል ግምት የሚሰጠው ዓይደለም። ይህ አስከፊ ተግባር ሁሉ የተፈጸመው በወያኔ መሪር አገዛዝ የተነሳ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

በ1983 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ለይስሙላ የተቀመጠው ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት በተከናውነው ሀገር አቀፍ ምርጫ በሕዝብ የተጠላውና ግፈኛው የወያኔ መንግሥት በምርጫው ሙሉ ለሙሉ የተሸነፈ መሆኑ የአውሮፓ ነጻ የምርጫ ታዛቢውዎች/Europian Independant Election Obserevers/ ለዓለም ያሳወቁት ግልጽና የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ ሳለ በጦር መሳሪያ አስገድዶ መግዛት የባህሪው የሆነው ወያኔ ተሸናፊነቱን ሳይቀበል በጠበኛ አፈሙዝ አስገድዶ የኢትዮያን ሕዝብ ነጻ የምርጫ ድምጽ ከመቀማቱም በላይ የሕዝብ ምርጫና ድምጽ ይከበርልን በማለት ብሶታቸውን ያሰሙትን አንድ መቶ ዘጠና ሦስት የሚደርሱ ንጹሃን ወገኖች በአደባባይ ጨፍጭፏል። በወቅቱ የዓለም ማኅበረሰብን ባሳዘነ መልኩ ሰላሳ ሺህ የሚደርሱ ዜጎችን ሰባዊ መብታቸውን በመንፈግ በግፍ አስሮ አንገላቷቸዋል /Illegally Mass Arrest and Tortured /። በዚሕ አስከፊና ኣሳዛኝ ወቅት በድብደባ፣ በወባ እና በሌሎችም ተዛማች በሽታዎች ሕይዎታቸውን ያጡ ወገኖች ቁጥራቸው ብዙ ነው።

ቀጥሎም በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ በመግባት በተለይም የኢትዮጲያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስን ስልጣን በመቀማት ፓትርያርኩን በኃል አስገድዶ በማውረድ በግፍ ሀገራችውን ጥለው እንዲሰደዱ አድረጓል። ከዚያም ለዝመናት ተግባብተውና ተቻችለው በሰላምና በፍቅር በሚኖሩት የሀገሪቱ ሁለት አቢይ የሃይማኖቶች ፓልቲካዊ ጣልቃ ገብነት በማሳየት በደቡባዊ የሀገራችን ክፍል ካድሬዎቹን ልኮ ባስነሳው እረብሻ በስልምናው ሃይማኖት ውስጥ የተነሱ አክራሪያን ሙስሊሞች በክርስቲያን ወገናቸው በጽሎት ላይ እንዳሉ አደጋ በመጣል በሰይፍ እንዲታረዱ አድርጓል፣ አብያተ ክርስቲይናትም ተቃጥለዋል።

በዚህ በ23 ዓመት የጭቆና ዘመናት ውስጥ በሀገራችን እና በዜጎቻችን ላይ ወያኔ ያልተደረገ ነገር የለም። ታሪካዊ ቅርሶች ተመዝብረዋል፣ ጥንታውያን ገዳማት በማፍረስ አጽመ ቅዱሳንን አፍልሰዋል፣ ሕዝብ በጎሳዊ ቋንቋ በሃይማኖት በጠባን ዘረኝነት በመከፋፈል እርስብራሳቸው እያጨፋጨፈ ይገኛል።

ድርጅቱን የሚቃወም ኢትየጵያዊ ዜጋ ሁሉ በሀገሩ በነጻነት የመኖር፤የመሥራት መብቱን በመንፈግ ለችግርና ለሲቃይ እየዳረገው ይገኛል፤ ለመጥቀስ ያህል በአርባ ጉጉ፣አሩሲ የአማራ ተወላጆችን ከነሕይዎታቸው ገደል ውስጥ ተጨምረዋል ፤በወለጋና በጅማ በግፍ እንደከብት ታርደዋል፣ አሁን በቅርቡ በደቡብ ህዝቦች ክልል በቤንሻጉልና የአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰውን እንግልት ስቃይ ሞት ሁሉ በዓለም የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን በኢሳት፤ በጀርመን ሬርዮ፤ በአሜሪካን ሬድዮ፤ በመሳሰሉት ሁሉ የተዘገበው ከበቂ በላይ ማስረጃ ቢሆንም በመገናኛ ብዙኃን ያለተዘገብ ወያኔ በኢትዮጵያዊያን ዜጎች የሚፈጽመው ወንጀል እጂግ በጣም መጠነሰፊ ነው።

የሀገራችን የሱዳን አዋሳኝ የሆነውን ለም መሬት ከህግራችን የታካዊ ጠላት ከሆነው እና በአረቦች ከሚረዳው ከወንጀለኛው የአልበሽ መንግሥት ጋር በመመሳጠር 1600 ስኩየር ኪሎ ሜትር ቢያንስ ከቤልጀም ሀገር ጋር እኩል ስፋት ያለው መሬት ለሱዳን አሳልፎ ስጥቷል። በቅርቡ አልጃዚራ ቴሌ ቪዥን እንደዘገበው በኢንቨስትመንት ስም እጂግ በጣም እርካሽ በሆነ ገንዘብ ለሕንድ፣ለፓኪስታን፣ ለአፍጋኒስታን ባልሀብቶች የሚሸጠው ለም የሀገራችን መሬት እጅግ በጣም ብዙ ነው። ይህ ሁሉ ተግባር የሚከናወነው የሀገሪቱ ዜጎች በግፍ እየተፈናቀሉ እና እዲሰደዱ በማድረግ ነው።

በጠቅላላው በስልጣን ላይ ያለው ጠባቡ የወያኔ መገሥት በሀገርና በዜጎች ላይ የሚፈጽመው ግፍ እጂግ በጣም ከባድና መጠነ ሰፊ ነው።

የሀገራችን ታሪክ እንደሚያስረዳው ቀደም ሲል የነበሩት ኢትዮጵያ መሪዎች የህግራቸውን ዳርደንበር አስከብረውልን እሰከ ወያኔ መንግሥት መባቻ ደረስ አቆይተዋል። ይህታሪካዊ አድራ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሆኖ ነው። ዛሬ ሀገራችን በአራቱም ማዕዘን እንደ ፍየል ሌጦ ተወጥራ ዳር ድንበርዋ እየፈረሰ ለም መሬትዋ ርካሽ በሆነ ዋጋ እየተሸጠ፤ ዜጎቿ እየተገደሉ፣ በግፍ የእተሰደዱ፣ ለርሃብና ከፍተኛ ለሆነ ችግር እየተጋለጡ እያየን እየሰማን እኔ ምንቸገረኝ ብለን የምንቀመጥበት ጌዜና ስዓት አለመሆንን በከፍተኛ ደረጃ መረዳት የኖርብናል።

ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የዘር፣የቋንቋ ለዩነት አስወግዶ እራሱን በየአለበት በማደራጀት አንድነት በመፈጠር የአባቶቻችን አድራ የሆነችውን ኢትዮጵያ ሀገራችን የሚያፈራርሰውንና ሕዝባችን የሚበታትነውን ማቆሚያ ለሌለው ከፈተኛ ችግር የሚዳርገውን የጋራ ጠላታችን ወያኔን ለመታገል ቆርጠን የመነሳት ወቅት አሁን የኖርብናል።

ኢትዮጵያ በአንድነትዋ ለዘላለም ትኑር!!

ተድላ ጌትነት ጀርመን